# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 1 ቁጥር 5　　　　ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፪ ሺህ ፮ ዓ.ም.

## ሜይ ዴይና ዝክረ ሰማዕታት

***የ«ያ ትውልድ ተቋም»ን ድረ ገጽ ይፋ መደረግ 2ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ***

የሜይ ዴይ እንቅስቃሴ ቅኝቱን የጀመረው በ18ኛው ምዕተ ዓመት ገደማ የሽካጎ ሄይ ገበያ ግርግር (Chicago Haymarket Incident) እየተባለ በሚታወቀው የሽካጎ ሄይ ገበያ ሠራተኞች (Chicago haymarket employee) ባደረጉት በቀን የ8፡00 ሰዓት የሥራ ሰዓት ሕግ ጥያቄ ነው። በዚህም ሰልፍ ላይ ከፖሊስ ጋር በተደረገው ግጭት ሳቢያ በፖሊስ ተኩስ ቁጥሩ ያልታወቀ ሰራተኛ ሕይወቱን አጥቶአል።

በ1889 እ.ኤ.አ. ገደማ የፓሪሱን አብዮት የመቶ ዓመት መታሰቢያ በማድረግ ፓሪስ ላይ የተሰየመው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ ጉባዔ ይህንን ቀን ሚያዝያ 23 (May 1st)ን የሽካጎን ሠራተኞች ትግል በማስታወስ፤ ይህ ቀን እንደ መታሰቢያነቱ የዓለም ሠራተኞች ትግል መታሰቢያ ቀን እንዲሆን አሳስቦ ሀሳቡ በዚህ ጉባዔ የደመቀ አድማጭ ሳያገኝ ቀረ።

ከዚህ ስብሰባ በኋላ በ1891 ጄኔቭ ላይ የተሰየመው ሁለተኛው ዓለም አቀፍ ጉባዔ ሜይ ዴይን (May Day) የዓለም ሠራተኞች የትግል መታሰቢያ ቀን እንዲሆን እውቅና ሰጠው። ከዚህ እውቅና በኋላ የዓለም ሠራተኞች በቀን የ8፡00 ሰዓት የሥራ ሰዓት ሕግን፣ የሠራተኛ ማሕበር የማቋቋም መብትን፣ እንዲሁም ሌሎች የሠራተኛ መብት የታገሉበትን ቀን የሚያከብሩበት፡ ለዓለም ሠራተኞች አጋርነቱን የሚገልጥበት ቀን በመሆኑ በሠራተኛው ሕዝብ ሰልፍ እና በትርዒቱ የሚያከብረው የሠራተኞች ቀን መሆኑን አብዛኛው የዓለም ሕዝብ ቀስ በቀስ እያወቀው መጣ ።

ይህ ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ በየካቲቱ 1966 አብዮት ምክንያት የመጣው የሜይ ዴይ አውደ በዓል በተከበረበት እና በኖረበት የክብረት ሕይወቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጭንቀት ደወል መታሰቢያ እያደረገ አልፎአል። በመሆኑም ይህ የኢትዮጵያው የሜይ ዴይ (May Day) የጭንቀት ደወል በተለይ የሚያዝያው 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በጨካኝነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት፤ በመልኩም ፍፁም አስቀያሚ ጭፍጨፋ የተካሄደበት ዕለት ነበር። በመሆኑም ድርጊቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ የስነ-ልቡናዊ ዘይቤ ላይ የጣለው ጥቁር መንፈስ፡ በማንኛውም ዘዴ የማይገፈፍ የክፉዎች ሁሉ ቀን የበላይ ነበር።

የሚያዚያ 21 ቀን 1969 ዓ.ም. በተለይ በአዲስ አበባና በተመሳሳይ መልኩ በሌሎች ክፍለ ሀገር ከተሞች በዓሉን በሰላማዊ ሰልፍ ለማክበር በወጡ ወጣቶች ላይ ደርግ የጥይት ሩምታ በመልቀቅ በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች ደም እንደጎርፍ የፈሰሰበት ዕለት ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» በዚህ ቀን በመላ ሀገራችን ለዴሞክራሲ መብትና ለሕዝብ መንግሥት ምሥረታ፤ የላብ አደሩና አርሶ አደሩ ቀዳሚ ፋና ወጊ በመሆን የተጨፈጨፉ ወንድምና እህቶቻችንን እየዘከርን በጊዜው ከነበረው የሰልፉ ሂደት የአንድን አካባቢ እውነተኛ ታሪክ ትረካ እናቀርብላችኋለን።

ያ ቀን ከጠዋቱ ጀምሮ ያ ያደኩበት የአዲስ አበባ ጀምበር፡ አዲስ አበባን ሳይመስለኝ እንደቀፈፈኝ ረፈደ። (ጢሞ)

ያን ለት ከፓርቲው (ኢሕአፓ) የሚመጣው መረጃ ሠልፉ ይደረጋል፡ አይደረግም እየተባለ ቢለዋወጥም የማታ ማታ ሠልፉ እንደሚደረግ ታወቀ። (ሳሙኤል)

ከቀኑ 9፡00 ሰዓት መምሕር ቤት፡ የሠልፍ ዝግጅት ተጀመረ።

1ኛ. ሠልፉ የሚሆነው ማታ ሆኖ የሚጀመርበት ሠዓት ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ሆነ።
2ኛ. ሠልፉ የሚነሳው ከአቡዋሬ ከ2ኛው እንሳሮ ሆቴል ፊት ለፊት ይጀምርና ውስጥ ውስጡን ተጉዞ፡ በልዕልት ዘነበወርቅ ትምህርት ቤት (የአሁኑ የካቲት 66) ጀርባ አድርጎ፡ በብላታ ትርፌ ሹምዬ ቤት በኩል፡ የግንፍሌን ወንዝ ተሻግሮ፡ ካዛንቺስ ቶታል ላይ ሠላማዊ ሠልፉ እንደሚያበቃ ተወሰነ።

ይህንን ድርጅታዊ መረጃ ይዘን ከሠልፉ መሄጃ መስመር በቀር የሠልፉን ሰዓት እና ቦታ ወደ ታች ለአባላት ለማስተላለፍ ተስማምተን ተለያየን።

ከቀኑ11፡00 ሰዓት

እንደ ገና ወደ መምሕር ቤት ተመልሰን ለሰልፉ የሚያስፈልግ ዝግጅት ማድረግ ጀመርን።

ዝግጅት ፦ ወቅታዊ መፈክር፣ መዝሙር፣ የድምፅ ማጉያ (ሜጋፎን) እና ባትሪ ማዘጋጀት።
ፕሮግራም ፦ ሠልፉን የምንመራው እኛ በመሆናችን፤ የሠልፉን ሥነ ሥርዓት እና የየራሳችን የስራ ድርሻ ምን እንደሚሆን ተነጋገርን። ከመሀል ሆኖ መፈክር እያሰማ ሠልፉን እንዲመራ (ሳሙኤል) ተመደበ። (ጢሞ) ከሠልፉ ፊት እንዲሆን እና የሠልፉን መሄጃ አቅጣጫ መስመር እንዲመራ፤ መምሕርና ቄሱ ከሠልፉ ኋላ በመሆን ሠልፉ እንዳይበተን መስመሩን እንዳይስት እና በሌላ ሜጋፎን ሠልፉን ማድመቅ ሀላፊነት ተደላደልን።

ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት

እንደተባባልነው ሠልፉ በሳሙኤል መሪነት ሜዳው መሀል ላይ ሆኖ "**ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት በአስቸኳይ ይቋቋም !**" ብሎ በድምፅ ማጉያው ሲጮህ ወጣቱ ከየጥሻው እየወጣ ከእንሳሮ ሆቴል ፊትለፊት ያለውን ክፍት ቦታ አጥለቀለቀው። «ለዘመናት» መዝሙር ያስተጋባ ጀመር።

“. . . ቢወቀጥ አጥንቴ
ቢንቀረቀር ደሜ
ላዲስ ሥርዓት ልምላሜ።
ፍጹም ነው ዕምነቴ
የትግሉ ነው ሕይወቴ . . .”

ጢሞ ፡ ከሠልፉ ፊት በሌላ ድምፅ ማጉያ ሳሙኤል የሚለውን እየደገመ ለሠልፉ በእጁ ምልክት እየሰጠ አቅጣጫውን አስያዘው። ሠልፉም ተከተለው። መምሕርና ቴሱም በበኩላቸው በሌላ ድምፅ ማጉያ የሳሙኤልን የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስትን ጥያቄ መፈክር እያሰሙ በሠልፉ ዙሪያ እንደ እረኛ ይራወጣሉ። ሠልፉ አቅጣጫውን እንዳይለቅ፡ እንዳይቆረስ፡ እየተከተሉ ወደ ፊት ይገፋሉ። ሠልፉም በደመቀና በተዋጣ ሁኔታ ወደ ፊት ተጓዘ። ወዲያውም የሠልፉ ድምቀትና ጩኸት፡ የሚዘመረው መዝሙር፡ የሚፈከረው መፈክር፡ የድምፅ ማጉያውን ድምጽ ዋጠው። እንደ ሰደድ እሳት አካባቢውን የዋጠው ሰልፈኛ የጋለ ስሜቱና የወኔው ጉብዝና ትንፋሽ ያካባቢውን አየር የአጋለው መሰለ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ውስጡን ተጉዘን፡ ልዕልት ዘነበወርቅ ትምህርት ቤት መዳረሻው ላይ ያለው መስቀልኛ መንገድ ላይ ስንደርስ ሠልፉ በትልቅነቱ፡ በግዝፈቱ፡ እንደ ደራሽ ውሃ ያገኘውን ሁሉ ጠራርጎ ይዞ የሚሄድ ትልቅ የሰው ሀይል ሆነ። የሠልፉ ጩኸት እያስተጋባ፡ አካሄዱ እንደ ጎርፍ ውኃ በጉልበት የሚተራመሰው ሠልፈኛ በዘነበወርቅ ት/ቤት ጀርባ፡ በ7ኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት፡ አድርጎ በብላታ ትርፌ ሹምዬ ቤት ጀርባ አልፎ በግንፍሌ ወንዝ ላይ፡ በአስፋ ወሰን 1ኛ ደረጃ ት/ቤት (የአሁኑ ምሥራቅ ጎህ) ጐን ጐኑን፡ ካዛንችስ ቶታል ሲደረስ የሠልፈኛው መዝሙርና መፈክር እያስተጋባ ካዛንቺስን አደበላለቀው። ይህ ሰልፍ በደረሰበት ሁሉ እንደደራሽ ጎርፍ ያገኘውን ሁሉ እየዋጠ ገዝፎ እዚህ የደረሰው ትዕይንተ ህዝብ ሲታይ፡ ቤቱ የቀረ ወጣት ያለ አይመስልም ነበር። ይህ የሰው ጎርፍ፡ ካዛንቺስን ያጥለቀለቀው ለ15 ደቂቃ ያህል መፈክር ሲያሰማ ቆይቶ ለዘመናትን ዘምሮ ሲያበቃ፡ ሠልፉ በዚሁ እንዳበቃ ተነግሮ፡ ሌላ ሠልፍ ማድረግ በጥብቅ የተከለከለ ለመሆኑ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ ሠልፉ ተበተነ።

ሰልፉ ካበቃ በዋላ ሁሉም ወደየቤቱ ተመለሰ። ሠልፉ እስቲበተን እዛው የቆዩትም ጢሞ፣ ቴሱ፣ ሳሙኤል እና መምሕር፡ መምህርን ቤቱ ድረስ በመሸኘት እና ድምፅ ማጉያዎቹን በመደበቅ በታላቅ ደስታ፡ በታላቅ ድል ወደ የቤታቸው ገቡ።

ሚያዚያ 22 ቀን 1969 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት

ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን እንድንገናኝ ቀጠሮ ስለነበረን፡ ቤተ ክርስቲያን ተሳላሚ መስዬ ወደዚያው እሄዳለሁ። ጠዋትነቱን በሰውነቴ ሰማሁት፡ በሳምባዬም ያንን የአዲስ አበባ ቀዝቃዛ አየር ማግ ማግ አደረኩት። ግን የትናንትናው ሙሉ ለሊት ተኩስ እና የውሻው ጩኸት ሲረብሸኝ ስለ አደረ ቅ..ፍ..ፍ.. ቅ..ፍ..ፍ.. እያለኝ ዑራኤል ደረስኩ። (ጢሞ) አንድ አንድ እያልንም ተገናኘን።

ሰልፉ እኛጋ እንደተሳካው በሌሎች ቀበሌዎች አለመሳካቱን መረጃ ደረሰን። በአንዳንድ አካባቢዎች ደርግ በደረሰው መረጃ መሠረት ገዳይ ኃይሎቹን አሰማርቶ ሰልፉ ሲጀመርና የጥይት ሩምታ ሲለቀቅ እኩል ሆነ። በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች "ፍጹም ነው እምነቴ" እንዳሉ ሕይወታቸውን ለትግሉ ሰጡ። አዲስ አበባ የደም ጐርፍ አጥለቀለቃት። አስፋልቶች በወጣቶች ደም ታጠቡ። በየአካባቢው ምሽቱ ደም በጠማቸው የደርግ ገዳዮች ሽብር ሆነ። ማን ይሙት ማን ይትረፍ መለየት እስኪያቅት ተኩስና ለቅሶ ለሊቱን አድረውበት፡ ለተረኛው ንጋት ለቀቁ።

ወደ ቤቴ ስመለስ፡ በማልፍበት አቅጣጫ ሁሉ የየቀበሌው ነዋሪ በተለይ ሴቶቹ ነጠላ እንኳ ሳይደርቡ በለሊት ልብሳቸው ጸጉራቸው እንደቆመ ደረታቸውን እየመቱ፡ ወደ ሰማይ እጆቻቸውን እያወራጩ በመረበሽ ይሯሯጣሉ። ወንዶቹ በየበራፉቸው ላይ በዝምታ ቆመው እንደ ጸሎተኛ አንዴ ወደ ሰማይ፡ አንዴ ወደ መሬት አንገታቸውን እያደረጉ፡ የልጆቻቸውን ሞት ይዞ የሚነፍሰውን ትኩስ ወሬ በፍርሀት ይጠብቃሉ። አንዱን ቀበሌ አቋርጬ ወደ ሌላው እያልኩ ሠፈሬ መዳረሻ ላይ ቀስ እያለ የሰዉ ሩጫ፡ ወደ ግርግር፡ ጩኸቱ ወደ ለቅሶ እያተለወጠ መጣ። ንጋቱም ወደ ረፋድ፡

ረፋዱ ወደ እኩል ቀን ሲደርስ፡ ድፍን የአዲስ አበባ ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ባገሩ፡ በሰፈሩ፡ በቤቱ ሙሾ ሊያወርድ ሀዘን ተቀመጠ። ነጠላዎች ተዘቀዘቁ፡ ቀሚሶች ጥቁር ሆኑ፡ እናቶች አባቶች ሀዘን፡ ቁጭትና እየዬ ዋጣቸው።

ከቀኑ 9፡30

መምህር ቤት፡ የደርግ መንግስት ትናንት ሌሊቱን "የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም !" ብሎ ሰልፍ የወጣውን ወጣት ገድሎ የገደለበትን የጥይት ዋጋ 250 ብር ማስከፈሉን ሰማን፡ ቤተሰቦች የልጆቻቸውን ለቅሶ መከልከላቸውን አየን። በዚያ ምሽት የከፍተኛ 15ቱ ቀበሌ 23 አብዮት ጠባቂ ሊቀ መንበር ፲/አ ሰሎሞን ከአንድ ቤት አራት ወንድማማቾችና (ደምሴ ብርሃኑ፣ ግርማ ብርሃኑ፣ ሞገስ ብርሃኑና ተፈራ ብርሃኑ) አንድ ያክስታቸውን ልጅ ከተኙበት አውጥቶ በመግደል ወላጅ እናትና አባት ያሏቸውን ብርቅዬ ልጆች በአንድ ምሽት ጭጭ አደረጋቸው። ግራዚያኒስ ከዚህ በላይ ምን አደረገ? የ1969 ዓ.ም. ሚያዚያ 21 ቀን ሠልፍ በአዲስ አበባ ብቻ እስከ 2000 ወጣቶች የተሰውበት ፡ ከግራዚያኒ ጭፍጨፋ ቀጥሎ አዲሱ የኢትዮጵያ ልጆች የእልቂት ምዕራፍ ሆነ።

ደርግ አንድ ብርቅዬ ትውልድ ጨረሰ። ሀገሪቷ በድህነት አቅሟ ለልማትና ለዕድገት የኮተኮተቻቸውን ልጆቿን ደርግ በላ። ለሕዝብ መብትና ነፃነት በግምባር ቀደምትነት የተሰለፉ ጀግኖች ልጆቿን፤ እምቡጥ አበባዎቿን ኢትዮጵያ ተነጠቀች። ክንዴ ልጇን አጣች። ኢትዮጵያዊነት ኩራቷን መለያ ክብሯን ጥቁር ድባብ አጠላባት። እምቢኝ ለመብቴ፣ እምቢኝ ለሀገሬ፣ እምቢኝ ለሕዝቤ ያለ ትውልድ በጥይት ተለቀመ። እየታነቁ ተገደሉ። በቁማቸው ከገደል አፋፍ ተወረወሩ። ወደ ባህር ተጣሉ። ሕጻናት ይህን አረመኔያዊ ድርጊት እያዩ እንዲያድጉ ተገደዱ። የዚህ አረመኔ አገዛዝ ጦስ ለዛሬም ተርፎ ብሔራዊ ስሜት እተሸረሸረበት፤ ያባት የእናቶቻችን ጀግንነት ተረት እሆነበት ዘመን ላይ አድርሶናል።

«ያ ትውልድ ተቋም» ልክ የዛሬ ሁለት ዓመት ለሀገራቸው ክብርና ለሕዝባቸው መብት ሲፋለሙ ክቡር ሕይወታቸውን ለሰዉት የኢትዮጵያ ጀግኖችና የያ ትውልድ ሰማዕታት መታሰቢያነት በ«ያ ትውልድ» ስም ያ ትውልድ ድረ ገጽን (www.yatewlid.com ወይም www.yatewlid.org) ለሕዝብ ይፋ ያደረግንበትን ሚያዝያ 23 ቀን 2004 ዓ.ም. ሁለተኛ ዓመት ስናከብር ታሪካችን ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ዘንድ በሩን በመክፈታችን ታላቅ ደስታ እየተሰማን ነው። ዛሬ አጠገባችን የሌሉትን ወንድምና እህቶቻችንን ቢያንስ ስማቸውንና ምስላቸውን እንደያዘ ለትውልድ የሚተላለፍ በየትም ሀገርና ቦታ ሆነው የሚያዩት ሐውልት አቁመንላቸዋልና ከተቀበልነው ቃል ኪዳን ጠብታዋን በማድረጋችን እየተደሰትን ከፊታችን የተደቀነውን ከባድ ኃላፊነት በትጋትና በሙሉ ስሜት ለመወጣት ቃል በመግባት ነው። አብረን ተሰልፈን፡ አብረን ጮኸን፡ አብረን ታግለን፡ አብረን ተሰቃይተን በተለያየ አጋጣሚ ዛሬ በሕይወት ያለን የዚያ ትውልድ አባላት ቢያንስ ልንዘክራቸው፡ ልናስባቸው ይገባል። እኛ ልንኖር እነሱ ሞተዋል። ደማቸውን ያፈሰሱ አጥንታቸውን የከሰከሱት "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም !" "የዴሞክራሲ መብት ያለገደብ ለሁሉም !" እየፈከሩ፡ "ደሀ ደሀ ምን ታየበት፤ እንዳይማር የሆነበት" እየዘመሩ፡ ለሕዝብና ለሀገር እንደጮሁ፡ መሆኑን በመመስከር ታሪካቸው ታሪካችን፡ ደማቸው ደማችን ነውና፡ እነሱን እያስታወስን አኩሪ ተጋድሏችንን ከታሪክ በራዦችና ጥላሸት ቀቢዎች በመጠበቅና በመከላከል ቀጣዩ አዲስ ትውልድ እነማን እንደነበርንና ምን ሠርተን እንዳለፍን ግንዛቤ በማስጨበጥ ከእኛ ሊቀስም ከሚችለው ትምህርት በመውሰድ ሀገሩንና ሕዝቡን አፍቃሪ ብቁ ዜጋ ይሆን ዘንድ ማዘጋጀት ይጠበቅብናል።

**ውድ የኢትዮጵያ ልጆችና ሕዝባችን !** በአፋኝ አገዛዞች በተለይም በፋሽስቱ ደርግ ኢሠፓ አገዛዝ ለዴሞክራሲያ መብትና ለሕዝብ መንግስት ምሥረታ የላብ አደሩ፣ የአርሶ አደሩ በጥቅሉ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ግምባር ቀደም አለኝታ በመሆን አምባገነኑን ፋሽስታዊ አገዛዝ ሲፋለሙ እስከወዲያኛው ያሸለቡ የኢትዮጵያ ልጆች በያ ትውልድ ተቋም ጥረት ገድላቸውና ታሪካቸው ከፍ ከፍ እያለ ነው። የ«ያ ትውልድ ተቋም» የኢትዮጵያ የትግል ታሪክ መረጃ ማሰባሰቢያ በሆነው ድረ ገጽ www.yatewlid.org ወይም www.yatewlid.com በየቦታው ወድቀው የቀሩ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ታሪክ እንዳይታወስ፣ እንዳይነሳ፣ እንደተዳፈነ ይቀር ዘንድ ምኞታቸውና ፍላጎታቸው የሆኑትን ዛሬ አሳፍሯል። በዚህ የሁለት ዓመት ጉዟችን ከጐናችን ሳትለዩ ላበረታታችሁን በሀገር ቤትም በውጪው ዓለም ላላችሁ የያ ትውልድ ወገኖችና አካላት፤ በተለያየ ወቅት ትብብር ላደረጋችሁልን የሚዲያ፤ የድረ ገጽ ወገኖችና በጠንካራ መሰረት በመሰባሰብ «ያ ትውልድ ተቋም»ን እዚህ ላደረሳችሁት የ«ያ ትውልድ ተቋም» አባላት በሞላ የዓለም ሠራተኞችን ቀን ሜይ ዴይ 2004 ዓ.ም.ን ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ላደረግነው ያ ትውልድ ድረ ገጽ ሁለተኛ ዓመት ክብረ በዓልና ዝክረ ሰማዕታት ቀናችን እንኳን በደህና አደረሳችሁ እያልን ቅን ትብብራችሁና ድጋፋችሁ አሁንም ከሰማዕታቱ ጐን ይሁን እንላለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» በዚህ የሁለት ዓመት ጉዟችን ምን አቅደን ስንቱ ተግባራዊ ሆነ? «ያ ትውልድ ተቋም» ይዞት በተነሳው ተልዕኮ ተግባራዊነት ላይ ያጋጠሙን አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮች ምንድናቸው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመቃኘት ቀጣይ የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት በተጨማሪ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ቡድኖች የሚደርሱንን አስተያየቶችና ምክሮች ግንዛቤ በመስጠት ለቀጣይ ጉዟችን በጠንካራ ስሜት በመዘጋጀት ቀኑን እንዘክረዋለን።

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ራዕይና ተልዕኮ ስኬታማነት ያሳለፍናቸው የሁለት ዓመት የሥራ ክንውናችን ምሥክር ነውና "ሜይ ዴይና ዝክረ ሰማዕታት" ስንል ጊዜያችን፣ ዕውቀታችን፣ ገንዘባችንና ኃይላችን የታሪካችን ምሰሶ የሆኑት ሰማዕታት ወገኖቻችን ናቸውና የ«ያ ትውልድን» ታሪክ ለቀጣይ ትውልድ ለማሸጋገር የምናደርገው ጥረት ቀጣይነቱን በማስመር ነው።

<<ያ ትውልድ ተቋም>>

ሚያዝያ 23 ቀን 2006 ዓ.ም. (May Day 2014)

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
Website : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
Facebook : yatewlid